# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 40

ህዳር 11 ቀን 2015 ዓም (20-11-2022)

ባለፈው ስርጭራችን በኢሕአዴግ ቤተሰቦች ወይም በወያኔና በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መካከል የተካሄደው ድርድርና የተደረሰበት ስምምነት ያንንም ተከትሎ በኬንያ ከተማ ናይሮቢ ውስጥ በሁለቱ ቡድኖች የጦር አበጋዞች መካከል የተደረሰበት ውል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ሰላምና ለኢትዮጵያ አንድነት ፋይዳ እንደሌለውና ተንገጫግጮ እንደሚቀር ተንብዬን ነበር።ያልነው አልቀረም ስምምነቱ ውሎ ሳያድር በክህደት መግለጫና ጫጫታ መልኩንና ይዘቱን ቀይሮ ብቅ ብሏል።እባብ ለእባብ ይተያያል ያልነው ተረታችን በተግባር ቁልጭ ብሎ ታይቷል።

ይሉኝታ ቢሱ የወያኔ ቡድን መሪዎች የፈረሙበት ቀለም ሳይደርቅ ድርጅትና ክልል ወክለን የገባንበት ውልና ስምምነት የለም፤ በማለት ማንን ወክለው ፕሪቶሪያና ናይሮቢ ከተማ ድረስ ሄደው እንደፈረሙ የሚያውቀውን ዓለም ለማደናገር ያለምንም ሃፍረት ሽንጣቸውን ገትረው ሲከራከሩ እንደሌላው ክህደታቸው ሁሉ ታዝበናል።የትግራይ ሕዝባዊ ሃይል እንጂ የህወሃት ጦር የለውም በማለትም የውዥንብሩን ጣራ ሰቅለውታል።በራሳቸው ስያሜ ሕዝቢ ወያኔ ሃርነት ትግራይ የሚለውን የታጠቀ ቡድን ከመጠሪያ ስሙ ነጥለው ለማጭበርበር ሲዳክሩ ማዬት የቡድኑ ማንነትና ይሉኝታ ቢስነት በግልጽ የታዬበት ነው። ይብላኝ ለወለደሽ እንዲሉ ይህን የመሰለ እኩይ ቡድን ከሃይማኖተኛው ማህበረሰብና ከትግራይ መሬት መብቀሉ ያሳፍራል።ለትግራይ ተወላጅ ትልቅ ሃፍረት፣ የታሪክና የስነልቦና ስብራት እንደሚያስከትል አያጠራጥርም።ምክንያቱም የወያኔ ቡድን ሁሉንም ነገር በትግራይ ማህበረሰብ ስም ስለሚሰራና ስለሚጠቀም ነው።የዚህን እኩይ ቡድን ተግባር የማይቀበለው የትግራይ ሕዝብ እስከዛሬ ድረስ ለተፈጸመው ወንጀል፣ደም መፋሰስና እልቂት ብሎም የሃገሩን አንድነት በሚቀናቀነው የፖለቲካ መስመር ከሌሎቹ ጋር ተባብሮ የገነባትን አገር ለማፍረስ በፈጸመው ደባና ሴራ ሊጠይቀው ይገባል፤በስሜ አትነግድ! በቃ! ብሎ ከጫንቃው ላይ አውርዶ ለፍርድ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ለአቅመ-አዳምና ሔዋን ያልደረሱ ልጆቹን ከጉያው እዬነጠቀ በማያስፈልግ ጦርነት በዬጦርሜዳው እዬማገደ ጭዳ ባስደረገበት፣ሽማግሌና አሮጊት፣ ወጣት ኮረዳ ሴትና ወንድ ከእለታዊ ተግባሩ አንስቶ ባስገዳጅ ጦርነት የአሞራ ሲሳይ ባደረገበት ወንጀሉ ሊጠይቀው ይገባል።ለሰላሳ ሁለት ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆነ ፍትሕን ተነፍጎ ለኖረበት ህይወቱ ተጠያቂ የሆኑትን ሁሉ በሕግ ፊት አቅርቦ ሊያሶስንባቸው ይገባል።የወንዜ ጅብ ይብላኝ በሚል ከንቱ ጎጠኝነት ፍትሕን ትርጉመቢስ ለማድረግ መተባበር አይኖርበትም።ለራሱና ለተተኪው ትውልዱ ሲል የፍትሕ አስከባሪ መሆን ይጠበቅበታል። በራሱና በራሱ ውስጥ ባሉት ወንጀለኞች ላይ ፍትሕን ሳያስከብር በሌሎቹ ወንጀለኞች ላይ ፍትሕ ቢጠይቅ ስለፍትሕ ያለው ግንዛቤ የተዛባ ይሆናል።አስቀድሞ ከቤቱ ቢጀምር ለሌላው ምሳሌና ምልክት ይሆናል።የወያኔ መሪዎች ከክህደት አቋም ላይ የደረሱት በራሳቸው ብቻ ሳይሆን ከኋላ የሚነዷቸው ምዕራባውያን በተለይም አሜሪካ እንደሆነች ከሚያንጸባርቁት አቋም ለመረዳት ይቻላል። ለውይይት እንዲቀርቡ እንዳደረጉ ሁሉ ስምምነቱ በሚፈልጉት መልክ ካልሄደና የሚሹትን ካላስገኘ ለማፍረስ ወደኋላ አይሉም።ጌታዋን የተማመነች ፍዬል ላቷን ከውጭ ታሳድራለች እንዲሉ የወያኔ መሪዎችም አድራጎት ከዚያ አይለይም።ለመሆኑ ለነጻነቱ ቀናኢ ከሆነው የኢትዮጵያ በተለይም የትግራይ

ሕዝብ ማህጸን እንደዚህ ያለ የባርነትን ቀንበር ለመሸከም የሚያስችል ጫንቃ የታደለ ቡድን ከዬት ተገኘ? የገዛ አገሩን ለማፍረስ መነሳት የተፈጥሮ እርግማን ወይም ጉድለት ሳይሆን አይቀርም እንላለን።

ከወያኔ መሳ ለመሳ የብዙ ወንጀሎች ፈጻሚና አስፈጻሚ የሆነው አንዱ የኢሕአዴግ አካል የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ቡድንም በማጭበርበር ከወያኔ ቢበልጥ እንጂ አያንስም።ከመምህሩ የደቀመዝሙሩ እንዲሉ ባለፉት አራት ዓመታት በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የተፈጸሙት ክህደቶች የ27 ዓመቱን የወያኔ ክህደቶች ያስከነዳሉ።የወያኔ ቡድን ህወሃት በሚል ስም የታጠቀ ሃይል ይዞ በግልጽ ሕዝብ ሲያሸብር ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ግን የአገር መከላከያ በሚለው በስተጀርባ አያሌ ግፍና ስቃይ ብሎም የሚዘገንን ግድያ የሚፈጽም አሸባሪ ቡድን በልዩ ልዩ ስም አሰማርቶ በታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ወንጀል ፈጽሟል፣ እዬፈጸመም ነው።ህወሃት ነጻ ትግራይን ለመመሥረት ሲዳክር ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ደግሞ ነጻ ኦሮሚያን ለመመስረት ደፋ ቀና እያለ ይገኛል።ሁለቱም ለዓላማቸው መዳረሻ አድርገው የወሰዱት የኢትዮጵያን መፈራረስ ነው።በዚህ የመጨረሻ ግብ ለመድረስ ሲሉ ከፊታቸው የሚቆመውን አገር ወዳድ ለመጨፍለቅ የዘረጉት መረብ ቀላል አይደለም። በኢትዮጵያዊነቱና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የማይደራደረውን ኢትዮጵያዊ በተለይም የአማራውን ማህበረሰብ ለማጥፋት ሁለቱም የጋራ ፍላጎታቸው ነው። ያንን ካልፈጸሙ ምኞታቸው እንደማይሳካላቸው ያውቁታል።ያንንም ካለፉት ሁለት ዓመት ወዲህ የሁለቱ የጥቅምና የሥልጣን ሽኩቻ በወለደው ግጭት ጊዜ በገሃድ አይተናል።የአማራውና የአፋሩ ከጠፋው ህይወት በተጨማሪ በንብረትና በከባቢው ላይ የደረሰው ውድመት የዚያ መንደርደሪያ ነው። ከደረሰው ውድመት መልሶ ለማንሰራራት ብዙ ዓመታት እንደሚጠይቅ ጥናቱ ያመለክታል።በነዚህ ኪሳራ ላይ ነው ሁለቱ ,አንድ የኢሕአዴግ ልጆች በመደራደር ስምምነት ላይ ደረሱ የተባለው።ዳሩ ሌባ ሲሰርቅ እንጂ ሲካፈል ስለማይስማማ የደረሱበት ስምምነት ትርጉመ ቢስ ሆኖ ለዳግም ጦርነት በዬፊናቸው የሚዘጋጁበትን ጥርጣሬና አለመተማመን ወልዷል።

ስምምነቱን ለመጣስ የወልቃይት ጠገዴንና የራያና አዘቦን ለም መሬት እንደምክንያት ባያቀርቡትም የስምምነቱ መቋጫ እንደነበር አይካድም።ይህንን የአማራውን ዋናና ወሳኝ የይገባኛል ጥያቄ በዚህም ሆነ በዚያ ብለው ለማድበስበስና ለማይገባው ወያኔ ለማስረከብ ሲባል ብዙ ተንኮሎች በመካሄድ ላይ ናቸው።የደጋፊዎቻቸውም ፍላጎትና አቋም ያው ነው።ስለሆነም በሕገመንግሥቱ መሠረት የማይሰጥ ከሆነ ከአማራው ጋር ወደለዬለት ጦርነት ለመግባት ዬተስማሙበት ለመሆኑ አብይ አህመድ በፓርላማው ላይ ተገኝቶ ስለወልቃይት የተናገረው በቂ ማስረጃ ነው።አብይ አህመድ በፖለቲካው በኩል ለማስፈጸም ሲንቀሳቀስ ወያኔዎቹ በጦር ሜዳ ነጥቀ ለመውሰድ ከባቢውን እንዲከቡ የጋራ ስምምነታቸው እንደሆነ በገሃድ እዬታዬ ነው።

ወልቃይትን ከአማራው እጅ ነጥቆ ለማስረከብ ባቀደው ሴራው በፓርላማ ተገኝቶ ሲናገር በወልቃይት በኩል የያዝነው አቋም የለም፤በውይይቱም ላይ አልቀረበም፣በጉልበት የተነጠቀ በጉልበት ይመለስ ማለትም ትክክል አይደለም፤በሕግና በሕግ ብቻ ማለትም በሕዝብ ውሳኔ የሚታዬ ጉዳይ ነው። ለዚያም ነባሩ ሕዝብ በቦታው መመለስ አለበት ብሏል።በጠመዝማሚት አነጋገር ከወያኔ ጋር በጦር ሜዳ ለመሰለፍ ቦታውን የለቀቀውና በማይካዳራ ጭፍጨፋ ላይ የተሳተፈው ወንጀለኛ ስብስብ በነጻነት ተመልሶ እንዲሰፍርና የድምጽ ሚዛኑን እንዲደፋ አረንጓዴ መብራት ምልክት ሰጥቷል።በዚህም አላቆመም የወልቃይትን የአማራ ተወላጅ ከሌላው አማራ ለመነጠል የሄደበት መንገድ ሴራውን ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ወልቃይቴ የትም ቢኖር የትም ወልቃይቴ ነው፤ አውስትራሊያም ሆነ አውሮፓ፣አሜሪካም ሆነ ሌላው አገር የሚኖረው ወልቃይቴ፣ያው ወልቃይቴ ነው በማለት ለወልቃይት ተወላጆች እውቅና የሰጠ መስሎ አማራነታቸውን የገፈፈበት አገላለጽ ነበር።የጠራ አማርኛ ቋንቋ

ባለቤት መሆኑንም ሲገፈው በተወላገደ አማርኛና በተወላገደ ትግርኛ የሚናገር ነው በማለት ተሳልቆበታል።የዘፈን ዳር ዳሩ እንደሚባለው ይህችን መሰሪ አገላለጽ ጎትቶ ያመጣው የወልቃይትን ሕዝብ ከሌላው ወንድሞቹ ለመነጠልና ያሰበውን ለማድረግ በማሰብ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው። የወልቃይት ጠገዴም ሆነ ራያና አዘቦ የቦታ ስሞች እንጂ የማንነት ስያሜዎች አይደሉም።ቦታዎቹ ሲወርድ ሲዋረድ የአማራው ማህበረሰብ አጽመ-እርስቶች ናቸው። ወልቃይትና ጠገዴ ጥንት የቤጌምድር አሁን የጎንደር ክፍለሃገር አካል ናቸው።ራያና አዘቦም የወሎ ክፍለሃገር አካላት ናቸው። ወያኔ በሚቆጣጠረው በጎሰኞች የክልል አወቃቀር ምንም እንኳን ለ27 ዓመታት በወያኔ ተነጥቀው የቆዩ ቢሆንም የአማራው ክልል ይዞታዎች የነበሩና መሆንም እንዳለባቸው የታሪክ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ።የወያኔ አመራር አባላትም አይክዱትም። በነዚህ ቦታዎች ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጥንትም ሆነ ወደፊት የከባቢውን ሕዝብ ባሕልና ወግ፣ማህበራዊና ሰላማዊ ግንኙነት እስካከበረ ድረስ የመኖርና ሥርቶ ሃብት የማፍራት መብቱ የተከበረ ነው።

በሁለቱ መካከል የሚገኝ ስምምነት በጋራ አገራችንን ለማፈራረስ፣ ሕዝቡንም በባርነት እዬገዙና እየከፋፈሉ ለማጫረስ እንጂ ለተሻለ ሰላምና እድገት፣ለአገርም አንድነትና ልዑላዊነት መከበር እንደማያበቃ የሁለቱን እኩይ ጸባይና ተፈጥሮ የሚያውቅና ፖለቲካም የሚረዳ የሚመሰክረው ሃቅ ነው።ይህንን ሴራ ለማከሸፍ ሁሉም አገር ወዳድ በአንድ ጣራ ሥር ተሰልፎ አገር አድን ትግሉን ማካሄድ ይጠበቅበታል።ቀደም ብለን ደጋግመን እንደገለጽነው ነገር ዓለሙ ከቁጥጥር ውጭ ሳይሆን ሳይቃጠል በቅጠል ብሎ ለመነሳት ጊዜው አሁን ነው እንላለን።አለበለዚያ ጅብ ከሄደ ይሆንና የዛሬው ባላገር ነገ አገረቢስ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው።አቅጣጫውም ያንኑ ያመላክታል።

ዓላማቸውን ከዳር ለማድረስ ወያኔ የጦርነት ነጋሪት ሲጎስም በኦሮሚያ ውስጥ በክልሉ ባለሥልጣናትና በሌሎቹ የኦሮሞ ድርጅቶች ትብብርና ተሳትፎ የሚንቀሳቀሰው አሸባሪ ቡድን ሃይሉን አጠናክሮ ቦታዎችን ለመቆጣጠር ከመቻሉም በላይ ብዙ የአማራ ተወላጆችን በዬቀኑ እያደነ በመጨፍጨፍ ላይ ተሰማርቷል።ይህንን ወንጀለኛና ኢሰብአዊ ድርጊት የሚፈጽም ቡድን አብይ አህመድ ለይምሰል በቃላት እያወገዘ ሲያማልል የሚመራው ድርጅት ኦሕዴድ መረጃ፣ትጥቅም፣ ስንቅም ከማቀበል ወደኋላ አላለም።ሰሚ ያጣው የንጹሃን የድረሱልን ጥሪም ምላሽ አላገኘም።ደማቸውና እምባቸው ከመፍሰስ አላባራም።ሞተውም እንደሰው የመቀበር ዕድል አላገኙም።እንደቁሻሻ በአካፋ ተዝቀው የተቀበሩት በጫካ ተጥለው የአውሬ ቀለብ ከሆኑት በላይ ዕድለኞች ሆነው የሚቆጠሩበት ጊዜ ላይ ነን።ይህ በሚካሄድባት አገር ውስጥ ነው ስለልማት፣ብልጽግና፣ የአረንጓዴው ትርክት፣የስንዴው ምርት፣ የኑክሌር ሃይሉ፣የጠፈር ላይ የሳተላይት መንኮራኩር ማምጠቅና ፣የሳተላይት መንደር፣የስድስት ኮከብ ሆቴሎችና መዝናኛ ቦታዎች ግንባታ ኧረ ምኑ ቅጡ! በዜና አውታሮችና ተከፋይ ውታፍ ነቃይ ጋዜጠኞች እንዲሁም እበላ ባይ ሆድ አደሮች ሲፈበረክና ሲስተጋባ የሚውለው።

ወደ ሳምንቱ አዬሩን ወደዋጠው የአብይ አህመድ የፓርላማ ውሎና ያደረገው አወዛጋቢ ንግግሩ ስንመለስ የታዘብነውን ለመግለጽ እንወዳለን።

ፓርላማ ሲባል በሕዝብ ተመርጠው የአገርን ሕግና ሥርዓት በመንደፍና በማስከበር፣ በዴሞክራሲ ምርጫና የሕዝብ ውሳኔ ስልጣን የያዘውን የመንግሥት አካላትና ብሔራዊ ተቋማትን የእለት ተእለት ተግባር የሚከታተሉ፣በፈለጉበት ወቅት በስልጣን ላይ ያለውን የመንግሥት ተጠያቂ ጠርተው በጥያቄ የሚያፋጥጡ፣መንግሥትና መሪዎቹ የተጣለባቸውን አደራ ካልጠበቁ ከሥልጣናቸው የማሶገድ መብት እንዳላቸው የሚያውቁና የሚጠቀሙበት፣ለገቡለት ቃል ኪዳን ተአማኒ፣አገር ወዳዶች የሚሳተፉበት ትልቅ ተቋም ነው።በአገራችን ውስጥ ፓርላማ የመንግሥት የግል ተቋም፣በመንግሥት ፍላጎት የሚሽከረከር፣የመንግሥትን እንቅስቃሴ ደግፎ የሚያጨበጭብ፣ለሕዝቡ ሳይሆን የመንግሥት ልሳን

የሆነ፣በደመወዝና በልዩልዩ ጥቅም የተገዙ ሆድ አደሮች የሚሰበሰቡበት ትልቅ አዳራሽ ነው።ግባ ውጣ የሚባል መንጋ የሚጠቀጠቅበት በረት ነው ማለቱ ይቀላል።እንዳጋጣሚ ሾልከው የገቡ ወይም ከጊዜ በኋላ ህሊናቸው ወቅሷቸው የሕዝቡን ፍላጎትና ጥቅም የሚገልጹ ጥቂቶችም ሊኖሩ እንደሚችሉ በዬጊዜው በሚቋቋሙት ፓርላማዎች ታዝበናል፣ቁጥራቸው አናሳ በመሆኑና የመንግሥቱ መሪዎች ባላቸው ከፍተኛ የባለቤትነት ተጽእኖ በነዚህ ላይ የሚደርሰው ውርጅብኝና የበቀል እርምጃም ቀላል እንዳልሆነም የማይካድ ነው።አንዳንዶቹም በፍርሃትና በጥቅም ሲያሸበርኩ ለመታዘብ ችለናል።ይህንን በመሰለው ፓርላማ ስብሰባ ላይ ነው አብይ አህመድ ማክሰኞ ሕዳር ቀን 2015ዓም ቀደም ሲል ፕሬዚዴንት ተብዬዋ ሳህለወርቅ ዘውዴ በመስከረም ወር የፓርላማ መክፈቻ ላይ ያደረገችውን የመክፈቻ ንግግር ተከትሎ ማብራሪያ ለመስጠት ተገኘ የተባለው።

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣ 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ፣4ኛ መደበኛ ስብሰባ በሚል መለያ በተሰናዳ ስብሰባ ላይ ከፓርላማ አባላት ለቀረበለት ጥያቄ ከተናገራቸው መካከል አንዳንዶቹን ነቅሰን ብናወጣቸው ይህንን ይመስላሉ።በጣም የሚገርመው ግን ሁሉም ጠያቂ ጥያቄውን ከመሰንዘሩ በፊት አንድ አይነት ካሴት የዋጠ ይመስል መግቢያ ያደረገው ንግግር አንድ አይነት መሆኑ ነው፤ያም " ክቡር ጠ/ሚኒስትር ዶር አብይ አህመድ ፕሬዚዴንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በመስከረም ወር ያደረጉትን የመክፈቻ ንግግር ተከትሎ ማብራሪያ ለመስጠት በመካከላችን በመገኘትዎ ላመሰግንዎ እወዳለሁ"የሚል ነበር።ይህ አባባል በራሱ ከላይ ስለፓርላማና አባላቱ የገለጽነውን ክብርና ድርሻ የሚቃረን ሆኖ አገኝተነዋል።

በዚያ መልኩ ከአስር የማይበልጡ አባላት ጥያቄያቸውን ያቀረቡ ሲሆን ሁሉም የጀመረው አብይንና የሚመራውን መንግሥት በማወደስ ቀጥሎም በተመረጠበት ከባቢ ያለውን ሁኔታ በሚመለከት ጉዳይ ላይ ነበር።አገራችን ያለችበትን አደገኛ ሁኔታ፣የንጹሃን ዜጎችን መጨፍጨፍና መፈናቀል፣የመንግሥትን ቸልተኛነት፣የሕገ መንግሥቱን ግድፈትና ለአንድነት ጸርነቱን፣አገሪቱ ባለችበት ደረጃ ባላስፈላጊ ግንባታ ላይ የሚባክነውን ገንዘብና ሃብት ፣የብድርና የእርዳታው ምንጭና ምክንያት፣የአገር ልዑላዊነት ተደፍሮ የሰሜኑ ድንበር መሬት በሱዳኖች ተወሮ መቅረቱን፣ለዘላቂ ሰላም ጸር የሆነው የሰፈነው የጎሳ ስርዓትና የክልል አወቃቀር እስከነ መመሪያው ሕገመንግሥት ተብዬው የጥፋት ሰነድ መሆኑን ደፍሮ የገለጸ የለም።ትንሽም ቢሆን በአዲስ አበባዋ የብልጽግና ተመራጭ በዶር ትዕግስት በኩል ስለአዲስ አበባ ማንነትና የሕዝቡ ጥያቄ የተነሳው የአብይ አህመድን የደም ግፊት የጨመረና የፊቱን ቀለም የለወጠው ጥያቄ ነበር።ጠያቂዋ በአዲስ አበባና በሰፈሯ በፈረንሳይ ሌጋሲዎን ወጣትና ነዋሪዎች መመረጧን ብትጠቅስም አብይ አንችን ሳይሆን ብልጽግናን ነው የመረጠው፣እራስሽን ከፍከፍ አታድርጊው በሚል መልኩ ለማሸማቀቅ ሞክሯል።አዎ ብልጽግናን ወክላ ነበር ለምርጫ የቀረበችውና የተመረጠችው።አሁን የያዘችው አቋም ቢኖራት ኖሮ ብልጽግና የሚመራበትን ሕገመንግሥት ተቀብላ ለምርጫ ባልቀረበች ነበር።ቢሆንም ከቀረ የዘገዬ ይሻላልና መጠዬቋ ያስመሰግናታል፤በአቋሟ ትዘልቅበት ይሁን አይሁን ወደፊት የምናዬው ይሆናል።ብልጽግናን አምኖ የተጠጋ መጨረሻው እንደማያምር ይህ አንድ ማሳያ ነው። ለትግስትና ለመሰሎቿ አይውሉ ውዬ ነው የሆነባቸው ለማለት እንደፍራለን።ሌላው ጠያቂ ከጎጃም በኩል የብልጽግና ተመራጭ ሆኖ የመጣው ሲሆን እሱም በፋኖና በዘመነ ካሴ ላይ ስለደረሰው መንገላታት መታሰርና መሰደድ ፣ዜጎች ወደ አዲስ አበባ አትገቡም ተብለው ስለመከልከላቸው፣ ገመድ ዘርግቶ መንገድ በመዝጋት ግብር ስለሚሰበስበው ወንበዴ ቡድን እንዲሁም የተመረጠበት አካባቢ ከልማት እንቅስቃሴው ተቋዳሽ አለመሆኑን የሚመለከት ነበር። የአብይ አህመድ መልስ የሚታሰረው ሕግ የጣሰ ብቻ ነው።እኛን በመስደቡና በመተቸቱ የታሰረ የለም።በማለት የሠራውን ወንጀል ሽምጥጥ አድርጎ ክዶታል።የታሰሩትንም አገር ወዳድ የዴሞክራሲ ታጋዮች ወንጀለኞች አድርጓቸዋል።ሌላው ቢቀር ሃሳብ የሰነዘሩትንና የመንግሥቱን ግድፈት ያሳዩትን በራሱ ትዕዛዝ ያሰራቸውንና ያሰቃያቸውን

እነ ተመስገን ደሳለኝን፣እነ ታዴዎስ ታንቱንና ሌሎቹን ከሕዝብ አይምሮ ለመፋቅ የሄደበት ክህደት ማንነቱን ይበልጥ አጋልጦታል።ሳናረጋግጥ አናስርም ያለውን ቃሉን ሽምጥጥ አድርጎ ሲክድ ላዩው እንደ ዶር ትእግስት ማማተብ ቀርቶ ለቆረጠ የፓርላማ አባል ከዚህ ቀጣፊ ጋር በፓርላማ ከምውል፣ይህ አጭበርባሪ በሚቆጣጠራት ከተማ ከምኖር ልብ ካለው ለትግል ወደ ጫካ አለያም ገዳም ልግባ ያሰኛል።ገዳምም ቢሄዱ ከአሸባሪዎች ጥቃት መዳን ባይቻልም ከተጠያቂነት መዳን ይቻል ይሆናል።

ስለአገራችን በሱዳን የመወረር ጉዳይ በጥያቄ የተነሳ ባይኖርም አብይ አህመድ ከሱዳኖች ጋር ጥሩ መቀራረብ አድርገናል፣በጋራ የምናድግበትን መንገድ ፈጥረናል በማለት የያዙትን መሬት እንዳጸደቀላቸው በሚያሳይ መልኩ ሸፋፍኖታል።ወትሮም ቢሆን ኢትዮጵያን ለመበታተን ከተሰለፈ ድርጅት መሪ የሚጠበቅ የተለዪ አቋም አይኖርም።ባለፈውም  ጊዜ  ኢትዮጵያ ለሰላም ስትል የማትሰጠው የለም ማለቱን ገልጸን ነበር ፤አሁንም የተደገመው ያው ነው።እሱ ሥልጣን ላይ ለመኖር ሲል አሳልፎ የማይሰጠው ያገር ክብርና  ልዑላዊነት አይኖርም።

በሌላዋም የፓርላማ አባል የሸኔ የትጥቅ ምንጩ ማነው?በማን ድጋፍና እርዳታ ከዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ በቃ?ለሚለው ጥያቄ አብይ የሰጠው መልስ ሸኔ ዓላማና መሪ የሌለው ፣በመዝረፍና በመግደል ላይ የተሰማራ  የአሸባሪ ስብስብ ነው በማለት በራሱ በሚመራው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የተደራጀና የሚደገፍ መሆኑን ለመካድ ሞክሯል። ድፍረትና ወኔ ቢሱ ፓርላማ አባላት ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ብለው በዝምታ  አልፈውታል።ይህ ዝምታቸው ግን ትልቅ የሕይወት  ዋጋ ሊያስከፍላቸው እንደሚችል ሊያውቁት ይገባል።አዲስ አበባ ዙሪያዋን በኦነግ ኦሕዴድ ጦር የተከበበችና ነዋሪዋ ሕዝብ ለመጨረሻው የጭዳ ሰይፍ የተጋለጠ  መሆኑን ሊያጤኑት ይገባል። የመስፋፋትና ከባቢውን ከነዋሪው የማጽዳት ዘመቻውም ከዚያ ጋር የተያያዘ መሆኑን ልብ ይሏል። ለዚያም ነው ከላይ ሳይቃጠል በቅጠል ያልነውን ጥሪ አሁንም የምንደግመው።

አብይ አህመድ በንግግሩ ያልነካካው ነገር የለም፣ነካክቶታል፤ግን በክህደትና በአስመሳይነት የተበከለ ነው።ከወያኔ ጋር ስለተደረገው ውይይት በምዕራባውያን የተቀናጀና በፍላጎታቸው የተመራ መሆኑን በመካድ የአፍሪካ ጉዳይ(ችግር)በአፍሪካውያን በሚለው ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ በምትከተለው ፣ ነጻነት፣እኩልነትና ፍትሓዊነት በሚለው ዲፕሎማሲ መርህ የተመራ ነው ሲል የምዕራባውያንን ድርሻና የአስገዳጅ ዱላ መመዘዙን ክዶታል። ለዓለም ባንክና  ለዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (World bank and IMF)ማጎብደዱን፣ አባሳንጆም ሆነ ኡሁሩ በምዕራባውያን በተለይም በአሜሪካኖች የሚነዱ መሆናቸውን ለማወቅ ነብይ መሆን አይጠይቅም።ፈጦና ገጦ የሚታይ ሃቅ ነው።

በዚህ ብዙ የውጭ አገር ታዛቢዎች፣ዲፕሎማቶች፣የሃይማኖት መሪዎች፣የውጭና ያገር ውስጥ ከበርቴ ነጋዴዎች በፓርላማው ሰገነት ላይ በተገኙበት ባደረገው ዲስኩር ብዙውን ጊዜ ያባከነው በኤኮኖሚው እድገት ላይ ነበር።የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ ሕዝቡን ባስመረረበት የኤኮኖሚ ቀውስ ፣ሥራ አጥ ወጣት በሚርመሰመስባት፣ከ9 ሚሊዮን በላይ ህጻናት ተማሪዎች የምግብ እርዳታ ለማግኘት በተገደዱባት፣በቀን አንድ ጊዜ እህል መቅመስ ከባድና ብርቅዬ በሆነባት አገር የኤኮኖሚ እድገታችን ከሰሃራ በታች ካሉት አገሮች መካከል በሶስተኛነት ሲመራ በቀሩት ያፍሪካ አገሮችም ውስጥ ካሉት ግንባር ቀደም አገራት መሃል ነች ሲል የራሱንና የደጋፊዎቹን፣ብሎም የተረኛ ሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ኑሮ የኤኮኖሚው መለኪያ አድርጎታል።ሁሉንም ችግር  ተቋቁማ ከዚህ የዕድገት ደረጃ ላይ መድረሳችን ዓለምን በሙሉ አስገርሞታል፤ከቶ የምትከተሉት ፖሊሲ ምስጢሩ ምንድን  ነው?እያሉ የሚጠይቁን አልጠፉም፤ኤኮኖሚስቶች ሳይቀሩ ተአምራዊ ምስጢር ሆኖባቸዋል በማለት ለማምታታትና፣የራሱን ብልህነት በማግነን የአድማጮቹን የንቃት ደረጃ የሚፈታተን ትንተና አቅርቧል።ጦርነቱና ኮሮና ለዚህ አይነቱ ዕድገት ለመብቃት ጠንክረን እንድንሠራ እረድቶናል ሲል ኮሮናና ጦርነቱን በአውዳሚነቱ

ሳይሆን በአልሚነቱ በተዘዋዋሪ አመስግኗል።በሁለቱም ቀውሶች ሳቢያ የብዙ ዜጎች ህይወት መጥፋቱንና ኑሮው መዛባቱን ከምንም አልቆጠረውም። ስለእድገቱ ማሳያ የሆነውን (Per capital income)የነፍስ ወከፍ ገቢ$ 1212 ዶላር ማለትም በቀላሉ አንድ ዶላር በ60 የኢትዮ/ብር ቢመነዘር አንድ ሰው በዓመት 72 ሽህ 720 ብር ወይም 6 ሽህ 60 ብር በወር ያገኛል ማለት ነው።ይህም ሁሉም ዜጋ በወር የአንድ የዩኒቨርሲቲ መምህር ከሚያገኘው ገቢ ጋር እኩል ነው እንደማለት ነው።በዚህም አላቆመም የአገሪቱ እድገት በኮሮና ጊዜ 6,4 ነበር ያለ ሲሆን ከበርቴ አገሮች ከዜሮ በታች በሆነ ኪሳራ ሲዳክሩ የነሱ ጥገኛ የሆነች አገራችን ከነሱ የተሻለ እምርታ ላይ ነበረች ማለቱ ነው።የወደፊቱም እድገቷ ከ7.5 በላይ እንደሚሆን ተንብይቷል። እውነት ቢሆን እድገትን የሚጠላ የለም፤ትግላችንም ለዚያ ነው።ግን ለዚያ ደረጃ ቀርቶ ዜጋ በፈለገበት ቦታ ሄዶ የመኖርና ሃብት የማፍራት መብቱን በሚነፈግበት ሥርዓት በሰፈነበት አገር እንደማይሆን እኛ ብቻ ሳንሆን ሌላውም ታዛቢ አይክደውም።

በሰው ጭንቅላት ውስጥ የሚብላላውና ከብዙ አቅጣጫ ነቀፋ የተሰነዘረበትን የ49.9 ቢሊዮን የቤተመንግሥት ግንባታ በሚመለከት ሳይጠዬቅ በኩራት የተናገረው ደፋሩ አብይ አህመድ የምን 49ቢሊዮን ብር ብቻ ያቀድነው ከ400-500 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ብዙ መንደሮችን፣ በሽህ የሚቆጠሩ መኖሪያና መሥሪያ ቤቶችን፣የመዝናኛ ቦታዎችን፣ ከስድስት ያላነሱ ሰው ሰራሽ ሃይቆችን ያካተተ የሳተላይት ከተማ ለመመሥረት ነው፤እቅዱም በመሬት ላይ ውሏል፣በቅርቡ የሚታይ ውጤት ነው እርማችሁን አውጡ ብሏል። ገንዘቡን በሚመለከት ከዬት መጣ እንዳይባል ቀድሞ ከመንግሥት ባጀት የወጣ ሳይሆን ከወዳጆቻችን በተገኘ እርዳታ ነው በማለት እንደለመደው ፓርላማ ሊጠይቀኝ አይችልም በሚለው ድምዳሜ ላይ አርፏል።የዚህና የሌሎቹም ከአገሪቱ ሕዝብ አቅምና ፍላጎት ውጭ ለሆኑት የመዝናኛ ቦታዎች፣ሆቴሎችና ቅንጡ መኖሪያ ቤቶች የአረቦች በተለይም የኢሚራቶች እጅ እንዳለበት ካለፈውና ብዙ ነዋሪ ከተፈናቀለበት ከጨርቆስ ከባቢ ፕሮጀክት ጋር ተነጥሎ የሚታይ አይደለም።አብይ አህመድ ያገሩን ደሃ ሕዝብ እያፈናቀለ ለባዕዳን ማስረከቡ፣መሸጡ ነገ እመሰርታታለሁ ለሚላት የኦሮሚያ አገር የኤኮኖሚ ጉልበት ለመፍጠር እንደሆነ ሁሉም ሊረዳው ይገባል።አረቦቹም የወደፊቱ ህይወታቸው ስጋት የተሞላበት በመሆኑ በቅድሚያ የሚኖሩበትን ቦታ ማመቻቸቱን ይመርጣሉ፤እስከዚያም ድረስ በሚኖሩበት አገራቸው የሙቀት ወቅት ወጣ ብለው በንጹህ አዬር የሚዝናኑበት ቦታና የሚያገለግላቸው የሰው ጉልበት በርካሽ ካገኙ ለመግዛት ዓይናቸውን አያሹም። አብይ አህመድ በማን አለብኝነት አገራችንን የግል ይዞታው ካደረጋት ውሎ አድሯል።የጨርቆስ ከባቢን የከተማዋ እንብርት ቦታ፣የታሪክ ገጽ የሆነውን የባቡር ጣቢያ(ላጋር)ለኢሚራቱ መሪ መሸጡን እንዲህ ሲል ገልጾ ነበር "እኔ እራሴ እዬነዳሁ የከተማዋን ቦታዎች ሁሉ ለምርጫ ሳሳዬው(እንደ በግ ተራ መሆኑ ነው) ቀልቡ ያረፈው በዚህ ቦታ ላይ ነው።3 ቢሊዮን ዶላር የሰጠኝ ሲሆን በቦታው ላይ ለነበሩት ሰዎች መኖሪያ አፓርትመንት፣ ታላላቅ ሆቴሎች፣መዝናኛ ቦታዎችና ሞሎች ይሠራሉ።"ይህንን ባለበት አፉ ስለገንዘቡ ማንም ሊጠይቀኝ አይችልም ሲልም ፓርላማውን ጸጥ አሰኝቶታል።ይህ አይነት ፓርላማ ነው በሃገርና በሕዝብ ስም የሚቀልደው።

የአብይ አህመድ የግንባታ ዲስኩር ለብዙ ወጣቶች የሥራ ዕድል ይፈጥራል በሚል ጉጉት ወጣቱን ለመደለል የሄደበት መሆኑ ግልጽ ነው።አገሩን ተነጥቆ ለነጣቂው በባርነት ለመኖር የሚሻ ወጣት ካለ እራሱን መመርመር አለበት እንላለን።

ሥራን በሚመለከትም እንዲህ ብሏል ሥራው አለ፣የጠፋው ሠራተኛው ነው።ዘመኑ ሥራ የሚፈልጉበት ሳይሆን ሥራ የሚፈጥሩበት ነውም ብሏል።ለመፍጠርም ሆነ ለመሥራት ሰላማዊ አገርና ተዟዙሮ የመሥራት መብት መከበር ይኖርበታል።ያንን የተነፈገ ሕዝብ ለፈጠራ የሚበቃ የተረጋጋ አይምሮና መንፈስ አይኖረውም።በኀሳ ማንነቱ የሚገደል፣የሚፈናቀል፣ ለሥራውም፣ለጥቃቱም፣ለጥቅሙም

በሚፈረጁበት አገር የተደላደለ ደስተኛ ህዝብና ትውልድ ሊኖር አይችልም።የሥርዓቱን ጥፋት ባልታደለው ሥራ አጥ ወጣት ላይ መለጠፍ ይቅርታ የሌለው ሃጥያት ነው።

በሌብነትም ላይ ፈገግ የሚያሰኝ ንግግር አድርጓል፣የሚመራው ሥርዓት የሌቦች መናሐሪያ መሆኑ፣ ሌባውና ዘራፊው የራሱ ድርጅት መሪዎች መሆናቸው ሲታወቅ፣ሌላው ቀርቶ መሬትና ሕንጻ እዬሰረቁ የሚቸበችቡና ለተረኛው የጎሳ አባላቸውና ለጥቅም አጋሮቻቸው የሚያድሉ ሌቦች ከተማዋን የሚቆጣጠሩ መሆኑን እያወቀ ሌብነትን የሚከላከልና ሌቦችን የሚያድን ኮሚቴ አቋቋምኩ ከሚለው በላይ የሚያስቅ ቀልድ አይኖርም።ቀልድ የሚያደርገውም የኮሚቴው አባላት ፣ተመስገን ጥሩነህንና በፍርድ ቤት በገንዘብ ዋስትና ስም የዜጎችን ኪስ የሚያራቁተው ሕጋዊ ዘራፊ፣ሌባ የፍትሕ ሚኒስቴር የመሳሰሉትን ማቀፉ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሌባን የሚያውቀው ሌባ ነው ተብሎ ሌባ ለፓሊስነት እንደሚመለመለው መሆኑ ነው። አሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ እንደሚባለው ሌብነቱ የከተማዋን ቦታ ከድሆች ነጥቆ ከሚቸበችበው አብይ አህመድና የከተማዋ አስተዳደር ባለሥልጣን ከነበረው ታከለ ኡማና ከአሁኗ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ይጀመራል። የፈረንጆቹ የልጆች መጽሔት የሚገልጸውን የአስራሁለቱን የሌቦች ታሪክ ይመስላል።የኮሚቴውን የሥራ ድርሻ ስንመረምር ለአብይ አህመድና ለስርዓቱ የማይመቹትን ለማሶገድ የተዘረጋ መረብ ሆኖ እናገኘዋለን።ያንንም በቅርቡ የምናዬው ይሆናል።

እዚህ ላይ ልናነሳ የምንወደው አብይ አህመድ 9ሚሊዮን ደሃ ተማሪዎችን እዬመገብን ነው ሲል በአገራችን የመጀመሪያው ደግና አሳቢ መሪ ሆኖ ለመቅረብ ሞክሯል።አዎ ህጻናት በችግር ምክንያት ከትምህርት ገበታ ላይ መቅረት የለባቸውም።ቁም ነገሩ ለምንና እንዴት ከዚህ ደረጃ ላይ ሊደርሱ ቻሉ?መፍትሔውስ ምንድን ነው?እስከመቼስ በእርዳታ የሰው እጅ እያዩ ይኖራሉ?የሚለው መልስ ማግኘት አለበት።እኛ እስከምናውቀው ድረስ ችግረኛ ተማሪዎችን መንከባከብ በአብይ ብልጽግና የተጀመረ አይደለም።ከሃምሳና ስልሳ ዓመት በፊት በንጉሱ ዘመን በዬትምህርት ቤቱ በተማሪው በተቋቋሙ የመረዳጃ ክበቦች የሚተዳደሩ ሻይና ብስኩት የሚሸጥባቸው ሱቆች በሚገባው ገቢ ለተማሪዎቹ ምግብ፣የትምህርት መሣሪያና ዩኒፎርም ይገዛላቸው ነበር። ከአሁኑ ጋር ልዩነት ቢኖር የተጠቃሚው ብዛት ብቻ ነው።በዛን ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 25-27 ሚሊዮን ሲሆን የአዲስ አበባ ነዋሪ አንድ ሚሊዮን አልገባም፤ግፋ ቢል 750 ሸህ ነበር።ትልቁ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ደሃ ከመኖሪያ ቀዬው አይፈናቀልም፣ዜጋም በፈለገበት ቦታ ሄዶ የመኖር፣የመሥራትና ሃብት የማፍራት መብቱ የተጠበቀ ነበር።በሚናገረው ቋንቋና በሚከተለው እምነት ተፈርጆ አይጨፈጨፍም፣ አይፈናቀልም ነበር።ባለፉት 32 ዓመታት የተገኘው ትሩፋት የዚያ ተቃራኒ ነው።

ከዚሁ ከትምህርት ቤት ግቢ ሳንወጣ አብይ አህመድ ስለትምህርት ተቋሙ በተለይም ስለዩኒቨርሲቲዎች ያለውን ለመጨመር እንወዳለን

እኛ ዩኒቬርሲቲዎችን አንገነባም፣ ትኩረት የምናደርገው የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው።ዩኒቨርሲቲዎች ወደፊት ከመንግሥት ይዞታ ይላቀቃሉ፤በራሳቸው ባጀት እንዲተዳደሩ ይሆናል ፣ ይህም ተጀምሯል ብሏል።በጣም የሚገርመው ከ500 ዓመት በላይ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ተቋም በገነቡት አገሮች የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች(State Unveresities)ባልተዘጉበት ዓለም ከ85 % በላይ ፊደል ያልቆጠረ መሃይም በሚኖርባት ፣ከ65 ዓመት ዕድሜ ያልበለጠው ዩኒቨርሲቲ የያዘች አገር፣ የንግድ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ይኖርባታል ማለት ሰውዬው ጭንቅላቱ በመሸጥና በመለወጥ የናወዘ መሆኑን ያሳያል።የትኛውስ የህብረተሰብ ክፍል ነው ልጁን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከፍሎ ለማስተማር የሚችለው?ለመደበኛ የአንደኛ ደረጃ ያልታደለ በሚሊዮን የሚቆጠር ደሃ ቤተሰብ ባለባት አገራችን

ልጆቹ ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት እንዳይበቁ ተፈርዶባቸዋል ማለት ነው።ምነው በንጉሡ ጊዜ የሴክተር ሪቪውን ታሪክና ያስከተለውን መዘዝ የሚነግረው ጠፋ?

በመጨረሻው ላይ ለማንሳት የምንወደው አንዳንድ ግለሰቦች  የምዕራቦቹን በተለይም የአሜሪካኖቹን ሴራና ደባ በሚቃወሙት በዬአገራቱ በሚኖሩት አገር ወዳዶች ላይ እንዴት ትቃወማላችሁ  በማለት የሚያስተላልፉት ትችት ትክክል እንዳልሆነና እንዲያስተካክሉ ለማሳሰብ እንወዳለን።የተወለድንበትን አገር መንግሥትና ፖለቲካ ስንቃወም የምንኖርበትን በዴሞክራሲ አምናለሁ የሚል አገር መንግሥት በሚያከናውነው ተግባርና ፖሊሲ መቃወም የዜግነትና የሰውነት መብታችን መሆኑን ሊያውቁት ይገባል።እኖርበታለሁ ተብሎ ፍትሕ በሚያጓድል መንግሥትና ሥርዓት ላይ አለመነሳት ወይም አለመቃወም፣በጭፍን እዬደገፉ ታማኝነትን በማሳዬት ለሚፈለግ ጥቅም ደጅ መጥናት ወይም ለበላበት ቤት ዘብ የሚቆምና የሚጮህ ውሻ መሆን ነው።ፍትህ የሚያጓድል፣ልዑላዊነትን የሚጥስ አካል የትም ሆነ የትም በፍትሕ ወዳዶች የሚወገዝ እንጂ የሚመሰገን አይደለም። ምንም እንኳን እያንዳንዱ ሰው እቆምለታለሁ ብሎ ላመነለት መንግሥት የመቆሙን መብት ብናውቅም፤እሱ ለሚወደው መንግሥት ቁሙ ወይም አትቃወሙ ብሎ የማለት ግን መብት እንደሌለው ለማሳሰብ እንወዳለን።

ከብዙ ውጣ ውረድ፣መንከራተትና ስቃይ በኋላ በተለመደው የገንዘብ ክፍያ በ30 ሺህ ብር ዋስትና ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ መፈታቱን ሰምተናል።ወትሮም መታሰር የሌለበት መሆኑን ደጋግመን ገልጸናል።እንኳን ለቤትህ፣ለእናትህና ለመላው ቤተሰብህ አበቃህ እንላለን።ቢወጣ እገ,ለዋለሁ ያለውም የተረኞቹ ጦር ሃይል ካሰበው አይመለስም የሚል ስጋት  ስላለን እራስህን ጠብቅ ለማለት እንወዳለን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህንን ብርቅዬ ልጁን እንዲጠብቀውና እንዲንከባከበው ጥሪ እናደርጋለን። በተመሳሳይም አዛውንቱ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ፣ከአማራው በላይ ለአማራው መብት የቆመውና ይህም እንደ ወንጀል ተቆጥሮበት በተደጋጋሚ ከህጻናት ልጆቹና ከባለቤቱ ተነጥሎ በእስር ቤት ለሚማቅቀው ታዲዎስ  ታንቱ ነጻነት ሁሉም እንዲጠይቅ ጥሪ እናደርጋለን።አሳሪውንም ሰውን በማሰር ሃሳብንና እውነትን ማሰር እንደማይቻል አምኖ በበቀል ያሰራቸውን የሕዝብ ልጆች በሙሉ ልቀቅ እንላለን።

የአንድነት ሃይሉ ግንባር ይጠናከር!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!

የከተት ጥሪ

ለእውነተኛ ፍትሕ፣እድገት፣ሰላምና አንድነት በሥልጣን ላይ ያለው የጎሰኞች ስብስብና የሰፈነው ሥርዓት መወገድ አለበት፣ለዚያም መመኘት ሳይሆን በቁርጠኝነት ተደራጅቶ መታገል ነው። ስለሆነም ይህንን የከተት ጥሪ ለማስተላለፍ እንወዳለን

አዋጅ!አዋጅ!አዋጅ!

በገዛ ሃገርህ የመኖር መብትህን ተገፈህ ፣እንደ አውሬ ታድነህ የምትጨፈጨፍ፣ ንብረትህን ተነጥቀህ ተፈናቅለህ በዬቦታው የተበተንከ፣ለችግርና ለመከራ የተጋለጥከ አጥቶ አደር የሆንክ ኢትዮጵያዊ ሆይ!

በቋንቋና በእምነትህ ተፈርጀህ የእልቂት ፍርድ የተጣለብህ፣ ሰሚና መከታ ያጣኸው ከርታታው ወገናችን ሆይ!

ሠርተህና ነግደህ ማደሩ እንደ ሃጢያት ተቁጥሮብህ በማንነትህ ምክንያት በግብርና በኪራይ ስም የምትበዘበዘው ነግዶ አዳሪ ሆይ!

በደሃዋ አገርህና በደሃው ወገንህ ላብ በተሰበሰበ ግብር ተምረህ ለቁም ነገር የበቃኸው ምሑር ሆይ!

በአንተ ላይ ጉዳት ባይደርስም ስለሰው ልጆች መብትና ደህንነት፣ለፍትሕ መከበር የምትቆረቆረው በሰውነትህ የደግ ልቦና ባለቤት የሆንከው ኢትዮጵያዊ ሆይ!

ይህንን የከተት አዋጅ ጥሪ ስማ!

አሁን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የመኖር ያለመኖር አደጋ ከፊት ለፊትህ ላይ ተደቅኗል።ያንን አደጋ የምታልፍበት ብቸኛው መንገድ በአንድነት ቆመህ መታገል ነው።በተበታተነ ትግል የተከፈለው አያሌ መስዋእትነት ካለህበት የስጋት ኑሮና መከራ ሊያወጣህ አልቻለም።ስለሆነም እንደ አንድ ሰው ተናጋሪ ፣ እንደብዙ መስካሪ ሆነህ ለሰብአዊ ክብርህ፣ለመብትህና ለአገርህ አንድነት በሚያረጋግጠው ትግል ላይ ተሰለፍ።

የሰፈነው የጎሰኞች ስርዓት ሊያጠፋህ እንጂ ሊጠቅምህ ስላልመጣ ከጫንቃህ ላይ አውርደህ ለመጣል ዛሬውኑ ተንቀሳቀስ!በትግል ሜዳ ላይ የተሰለፉትን አገር ወዳዶች ተቀላቀል፤በአካል፣በገንዘብ፣በምክር የምትችለውን አበርክት።በጎሰኞች የፖለቲካ እሳት እዬተጠበሱ ፣እዬታሰሩና እዬተፈቱ፣ሳይፈሩና ሳይንበረከኩ ድምጻቸውን የሚያሰሙትን አያሌ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ጥሪ ስማ።ከሞቀ ከቤታቸው ወጥተው ለአገርና ለወገን ሲሉ ዱር ቤቴ ብለው እዬተፋለሙ የሕይወት ዋጋ የሚከፍሉትን በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩትን ወገኖችህን ተቀላቀል።ጊዜው ጎራ ለይተህ የምትፋለምበት እንጂ በተረተረት ተሸንግለህ በተስፋ ተጃጅለህ እጅህን ለአሳሪ ሰንሰለት የምትዘረጋበት ጊዜ አይደለም።

የማሰብና የማስተዋል ችሎታህ ያልተዛባው፣ኢትዮጵያዊ ሆይ!

በወያኔ እኩይ ቡድንና አብይ አህመድ የተባለው መሰሪ በሚመራው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ስብስብ ጥምረት የተጠነሰሰልህን የጥፋት መርዝና አገር የመበታተን ሴራ ለማክሸፍና ያገርህን አንድነት፣ያንተንም በታሪክ የተመዘገበ ጀግንነት ዳግም ለማረጋገጥ ሆ ብለህ ተነሳ!በአንድ ግንባር ስር

ተሰልፈህ፣ሃይልህን አስተባብረህ በተባበሩብህ በውጭና በውስጥ ጣምራ ጠላቶችህ ላይ ዘምተህ ወደ መጨረሻው ከርሰ መቃብር ሸኛቸው።

ትልቁን ኢትዮጵያዊ ማንነትህን በሰፈር ማንነት ለውጦ በእድገትና በልማት ስም አፈናቅሎ መሬትህን ለውጭ ወራሪዎች የሚቸበችበውን አታላይ ከነተከታዩ መቀመቅ አውርድ።ለልጆችህ መንደር ሳይሆን አገር አውርስ፤የአያት ቅድመ አያቶችህን አደራ ጠብቅ!

ይህንን የከተት አዋጅ ሰምቶ ጥሪውን ተቀብሎ በሚችለው መንገድ በተግባር ያልተረጎመ ቢኖር ዘለዓለማዊ ባርነትን ለመቀበል የመረጠ ስለሆነ የሚጠብቀው የጌቶቹ ጅራፍና የመከራ ኑሮ እንደሚሆን ከወዲሁ ለማስጠንቀቅ እንወዳለን።ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ ብለንም እንተርትበታለን።